This VIS translation is out of date. When you give your patient this translation, also give them the up-to-date English version of it.
To get both, and to find out what was updated, go to www.immunize.org/vis

# የፖሊዮ ክትባት

## ማወቅ የሚያስፈልግዎት ነገር

### 1 ፖሊዮ ምንድን ነው?

ፖሊዮ በቫይረስ የሚመጣ በሽታ ነው። የልጅ (የአዋቂ ሰው) ሰውነት ውስጥ በአፍ በኩል ይገባል። አንዳንድ ጊዜ በጣም ጽኑ ሕመም አያመጣም። ፖሊዮ በቫይረስ የሚመጣ በሽታ ነው። የልጅ (የአዋቂ ሰው) ሰውነት ውስጥ በአፍ በኩል ይገባል። አንዳንድ ጊዜ በጣም ጽኑ ሕመም አያመጣም።

በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ፖሊዮ በጣም የተስፋፋ ነበር። ለፖሊዮ ክትባት ከማግኘታችን አንድ ዓመት ቀደም ብሎ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን በሽታው ሽባ ያደረጋቸውና የገላቸውም ነበሩ።

### 2 ለምን መከተብ ያስፈልጋል?

ያላንሰራራ የፖሊዮ ክትባት (አይፒቪ) (IPV) ፖሊዮን ሊከላከል ይችላል።

ታሪክ ፥ በ1916 ውስጥ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የነበረው የፖሊዮ ወረርሽኝ 6,000 ሰዎች ገድሎ ከ27,000 በላይ ሰዎችን ሽባ አድርጓል። በ1950 መጀመሪያ ዓመቶች ውስጥ በእያንዳንዱ ዓመት ከ20,000 በላይ የፖሊዮ በሽታ ምልከቶች ነበሩ። የፖሊዮ ክትባት የተጀመረው በ1955 ውስጥ ነበር። በ1960 ላይ የበሽታው ምልከቶች ቁጥር ወደ 3,000 የቀነሰ ሲሆን በ1979 ላይ 10 ያህል ብቻ ነበር። በዩኤስና በሌሎች ሀገሮች የፖሊዮ ክትባት መሳካት በዓለም አቀፍ ደረጃ ፖሊዮን ለማጥፋት ጥረትን አፋፍሟል።

ዛሬ ፥ በ20 ዓመት ውስጥ ምንም የፖሊዮ ምልከት በዩኤስ ውስጥ አልተገለጸም። ነገር ግን በሽታው አሁንም በጥቂት የዓለም ክፍል ውስጥ በዛ ብሎ ይገኛል። በክትባቱ የተጠበቅን ባንሆን ኖሮ በሽታው እንደገና ለመመለስ ከሌላ ሀገር የአንድ የፖሊዮ ምልከት ብቻ ወደዚህ ሀገር መግባት ይበቃው ነበር። በሽታውን ከዓለም ጨርሶ ለማጥፋት የሚደረገው ጥረት ከተሳካ ወደፊት አንድ ቀን የፖሊዮ ክትባት
አያስፈልግም ይሆናል። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ልጆቻችንን ማስከተብ ያስፈልገናል።

### 3 የፖሊዮ ክትባት መከተብ ያለበት ማነና መቼ ነው?

አይፒቪ (IPV) መርፌ ሲሆን እንደ ዕድሜ መጠን እግር ላይ ወይም ክንድ ላይ ሊወጋ ይችላል። የፖሊዮ ክትባት ሌሎች ክትባቶች በሚሰጡበት ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

**ልጆች**
አብዛኞች ሰዎች በልጅነታቸው ወቅት የፖሊዮ ክትባት ሊወጉ ይገባል። በሚከተሉት ዕድሜዎች ላይ ልጆች 4 መርፌዎችን ይወጋሉ ፥
✓ በ 2 ወር ዕድሜ ላይ አንድ መርፌ ✓ በ 6-18 ወር ዕድሜ ላይ አንድ መርፌ
✓ በ 4 ወር ዕድሜ ላይ አንድ መርፌ ✓ በ 4-6 ዓመት ዕድሜ ላይ አንድ የማጠናከሪያ መርፌ

**አዋቂዎች**
አብዛኞች አዋቂ ሰዎች በልጅነታቸው ወቅት ወርፌውን ስለተወጉ የፖሊዮ ክትባት አያስፈልጋቸውም። ነገር ግን ሦስት የአዋቂ ሰዎች ምድብ ለበሽታው የመጋለጣቸው ዕድል ከፍ ያለ ስለሆነ የፖሊዮ ክትባትን ለመወጋት ማሰብ አለባቸው።
(1) ፖሊዮ በተዘመተመት የዓለም ክፍል የሚጓዙ ሰዎች
(2) የፖሊዮ ቫይረስን ሊነኩ የሚችሉ የላቦራቶሪ ሠራተኞች
(3) ፖሊዮ የያዛቸውን ታማሚዎች የሚያክሙ የጤና ጥበቃ ሠራተኞች

በእነዚህ ምድቦች ውስጥ የሚገኙ ለፖሊዮ የመከላከያ ክትባት ያልተወጉ አዋቂ ሰዎች የአይፒቪ (IPV) 3 መርፌዎችን መወጋት ያስፈልጋቸዋል ;፡
✓ የመጀመሪያውን መርፌ በማንኛውም ጊዜ ላይ
✓ ሁለተኛውን መርፌ ከ 1 እስከ 2 ወራት በኋላ
✓ ሦስተኛውን መርፌ ከሁለተኛው መርፌ በኋላ ከ 6 እስከ 12 ወራት ውስጥ

በእነዚህ ምድቦች ውስጥ የሚገኙ ከዚህ በፊት 1 ወይም 2 የፖሊዮ መርፌ ተወግተው የነበሩ አዋቂ ሰዎች ቀሪዎቹን 1 ወይም 2 ወርፌዎች መወጋት ያስፈልጋቸዋል። የቀድሞዎቹ መርፌዎች ጊዜ ቅርብ ወይም ሩቅ ቢሆንም ባይሆንም።

**በአፍ የሚወሰድ የፖሊዮ ክትባት ፥ ባሁኑ ጊዜ አይታዘዘም**

ሁለት ዓይነት የፖሊዮ ክትባቶች አሉ ፥ አይፒቪ (IPV) ይህ በዩናይትድ ስቴትስ ባሁኑ ጊዜ የሚታዘዝ ሲሆን ሌላው በአፍ የሚወሰድ የፖሊዮ ክትባት (ኦፒቪ) (OPV) ጠብታዎቹ በአፍ የሚዋጡ ናቸው።

እስከ ቅርብ ቀን ድረስ ኦፒቪ (OPV) በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለሚገኙ ብዙ ልጆች ይታዘዝ ነበር። ኦፒቪ (OPV) ከሀገሬችን ውስጥ ፖሊዮን ለማጥፋት የረዳን ሲሆን አሁንም በብዙዎቹ የዓለም ክፍሎች ጥቅም ላይ ይውላል።

ሁለቱም ክትባቶች ለመሽታው መከላከያ ይሰጣሉ፥ ነገር ግን ኦፒቪ (OPV) በሽታው ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳይዛባ ለማገድ የተሻለ ነው። ይሁን እንጂ ጥቂት ሰዎችን (ከ2.4 ሚሊዮን አንድ ለሚሆኑትን) ኦፒቪ (OPV) ፖሊዮ ያሲዛቸዋል። በፖሊዮ የመያዙ አደጋ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ አሁን በጣም ያነሰ በመሆኑ ሐኪምዎ ሊያዙልዎት ከሚችሉት ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር በአፍ የሚወሰድ የፖሊዮ ክትባት ከአሁን ወዲያ ጥቅሙ ከጉዳቱ እንደማይበልጥ የበሽታው አዋቂዎች ያምናሉ። የፖሊዮ መርፌ (አይፒቪ) (IPV) ለፖሊዮ መንስኤ አይሆንም። እርሶ ወይም ልጅዎ ኦፒቪ (OPV) የምትወስዱ ከሆናችሁ የኦፒቪ (OPV) መደገሚያ ክትባት መረጃ ጽሑፍ ቅጅ እንዲሰጥዎት ጠይቁ።

በእነዚህ ምድቦች ውስጥ የሚገኙ ከዚህ በፊት 3 የፖሊዮ መርፌዎች ( IPV ወይም OPV) ተወግተው የነበሩ አዋቂ ሰዎች የአይፒቪ (IPV) ማጠናከሪያ መርፌ መወጋት ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

ለተጨማሪ መረጃ የጤና ጥበቃ አገልግሎት አቅራቢዎን ይጠይቁ።

This VIS translation is out of date. When you give your patient this translation, also give them the up-to-date English version of it.
To get both, and to find out what was updated, go to www.immunize.org/vis

## 4 አንዳንድ ሰዎች አይፒቪ (IPV) መወጋት የለባቸውም ወይም መቆየት አለባቸው።

የሚከተሉት ሰዎች አይፒቪ (IPV) መወጋት የለባቸውም ፤

- የአንቲባዮቲክስ ኒዮማሲን፣ እስትሬፕቶማሲን ወይም ፖሊማክሲን ቢ ለሕይወት የሚያሰጋ አለርጂ ኖሮባቸው የሚያውቁ ማናቸውም ሰዎች የፖሊዮ ክትባቱን መወጋት የለባቸውም።
- ለፖሊዮ ክትባት ኃይለኛ አለርጂ ያላቸው ማናቸውም ሰዎች ሌላ የፖሊዮ መርፌ መወጋት የለባቸውም።

እነዚህ ሰዎች መቆየት ያስፈልጋቸዋል ፤

- መርፌው በታዘዘላቸው ወቅት በመጠኑ ወይም በጽኑ የታመሙ ማናቸውም ሰዎች የፖሊዮ ክትባት ከመወጋታቸው በፊት ሕመማቸው እስኪሻላቸው ጊዜ ድርስ መጠበቅ ያስፈልጋቸዋል። እንደ ጉንፋን የመሰለ ቀላል ሕመም ያለባቸው ሰዎች መርፌውን ሊወጉ ይችላሉ።

ለተጨማሪ መረጃ የጤና ጥበቃ አገልግሎት አቅራቢዎን ይጠይቁ።

## 5 ከአይፒቪ (IPV) ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎች ምንድን ናቸው?

አይፒቪ (IPV) የሚወጉ አንዳንድ ሰዎች መርፌውን በተወጉበት ቦታ ላይ ሰውነታቸው የእብጠት ምልክት ይኖራቸዋል። ባሁኑ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው ክትባት ከፍተኛ ችግሮችን ማስከተሉ በፍጹም አይታወቅም፤ እናም አባዛኞዎቹ ሰዎች በክትባቱ ምንም ችግር የለባቸውም።

ይሁን እንጂ እንደ ማንኛውም መድሐኒት መርፌ ኃይለኛ አለርጂን የመሰለ ጽኑ ችግርን ሊያስከትል ይችላል። የፖሊዮ ክትባት ጽኑ ጉዳትን ወይም ሞትን የማምጣቱ አደጋ በጣም ትንሽ ነው።

## 6 ኃይለኛ የመርፌ መጣላት (ሪአክሽን) ቢኖርስ?

ምን ምልክትን ማየት ያስፈልገኛል?
ያልተለመዱ ሁኔታዎች ምልክቶችን ይመልከቱ ፤ እንደ ጽኑ አለርጂ፣ ከፍተኛ ትኩሳት፣ ወይም ያልተለመደ ባህርይ የመሰሉ ሁኔታዎችን።

ጽኑ አለርጂ የሚኖር ከሆነ መርፌውን ከተወጉ በጥቂት ደቂቃዎች ወይም ሰዓቶች ውስጥ ይሆናል። የጽኑ አለርጂ ምልክቶች የትንፋሽ ማጠር፣ መድከምን ፤ የድምጽ መገርነት ወይም ማቃተት፣ የልብ ተሎ ተሎ መምታት፣ የቆዳ መጉረብረብ፣ የማዞር፣ የቆዳ መገርጣት፣ ወይም የጉሮሮ ማበጥን ሊጨምሩ ይችላሉ።

ምን ማድረግ ያስፈልገኛል?

- ለሐኪም ይደውሉ፣ ወይም ወደ ሐኪም የሚወስድዎትን ሰው በአስቸኳይ ይጥሩ።
- ለሐኪምዎ ምን እንደሆነ ፤ የሆነበትን ቀንና ሰዓት ፤ እንዲሁም መርፌውን መቼ እንደተወጉ ይንገሩ።
- የ'ቫክሲን አድቨርስ ኢቨንት ሪፖርቲንግ ሲስተም' (ቪኤኢአርኤስ) (VAERS) ቅጽ በመሙላት ስለ አለርጂው ሐኪምዎን ፤ ነርስዎን ፤ ወይም የጤና ክፍልን ይጠይቁ። ወይም ይህን ሪፖርት በቪኤኢአርኤስ (VAERS) ዌብሳይት www.vaers.org በኩል ወይም 1-800-822-7967 በመደወል ሊያስገቡ ይችላሉ።

  *በቪኤኢአርኤስ (VAERS) የሕክምና ምክር አይሰጥም።*

የአለርጂ ምልክቶችን ማሳወቁ በክትባቶቹ ሊመጡ የሚችሉ ችግሮችን ባለሙያዎች እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

## 7 ብሔራዊ የክትባት ጉዳት መካሻ ፕሮግራም (The National Vaccine Injury Compensation Program)

አልፎ አልፎ እርሶ ወይም ልጅዎ ከክትባቱ ብርቱ አለርጂ ሲኖርባችሁ ለተጎዳው ሰው ሕክምና ለመስጠት ለክፍያው ሊረዳ የሚችል የፌደራል ፕሮግራም አለ።

ስለ ብሔራዊ የክትባት ጉዳት መካሻ ፕሮግራም (The National Vaccine Injury Compensation Program) ዝርዝር **1-800-338-2382** ይደውሉ
ወይም የፕሮግራሙን ዌብሳይት **www.hrsa.gov/bhpr/vicp** ይጎብኙ።

## 8 በተጨማሪ መማር የምችለው እንዴት ነው?

- ሐኪምዎን ወይም ነርስዎን ይጠይቁ። ስለ ክትባቱ ዝርዝር መረጃ ጹሑፍ ይሰጡዎታል ወይም ስለ ሌሎች የመረጃ ምንጮች ሃሳብ ይሰጡዎታል።
- ለአካባቢዎ ወይም ለስቴቱ ጤና ክፍል የክትባት ፕሮግራም ይደውሉ።
- ለ Centers for Disease Control and Prevention (CDC) ይደውሉ፣
  - **1-800-232-4636 (1-800- CDC-INFO)** ይደውሉ
  - የ National Immunization Program ዌብሳይት **www.cdc.gov/nip** ይጎብኙ።

**U.S. DEPARTMENT OF HEALTH & HUMAN SERVICES**
Centers for Disease Control and Prevention
National Immunization Program

Vaccine Information Statement
Polio (1/1/2000) - Amharic 42 U.S.C. § 300aa-26

Translation provided by Healthy Roads Media